AM



# የጣት አሻራዎች እና Eurodac

በቁጥር Nr. 603/ 2013 የደብሊን-ድንጋጌ፣ አንቀጽ 29 (3) (የአውሮፓ ኅብረት) ድንጋጌ (Artikel 29 (3) der Verordnung (EU) Nr. 603/ 2013) መሠረት በሕገ-ወጥ መንገድ በአባል ሀገራት ውስጥ ለሚገኙ የሦስተኛ ሀገር ዜጎች ወይም ዜግነት አልባ (ለሆኑ) ሰዎች መረጃ ስለመስጠት

በአንድ የደብሊን-ሀገር[1] ውስጥ በሕገ-ወጥ መንገድ የሚገኙ ከሆነ፣ የሚመለከተው ባለሥልጣን መሥሪያ ቤት የጣት አሻራዎችዎን ወስደው Eurodac ተብሎ ወደሚታወቀው የአሻራዎች ማከማቻ ማዕከል እንዲነጻጸሩ ሊልክ ይችላል። ይህ በዋናነት የሚያገለግለው እርስዎ ባለፉት ጊዜያት የጥገኝነት ማመልከቻ አስገብተው እንደሆነ ለማጣራት እንዲረዳ ብቻ ነው። የጣት አሻራዎችዎ በEurodac የመረጃ ማዕከል እንዲከማቹ አይደረጉም፤ ነገር ግን ባለፉት ጊዜያት በአንድ ሌላ ሀገር የጥገኝነት ማመልከቻ አስገብተው ከሆነ፣ ወደዚሁ ሀገር ተመልሰው እንዲላኩ ሊደረግ ይችላል።

የተወሰዱት የጣት አሻራዎችዎ የጥራት ችግር ያለባቸው ሆኖ ከተገኘ፣ ለምሳሌ ሆን ብለው በጣቶችዎ ላይ ጉዳት ያደረሱ በመሆኑ ምክንያት፣ እንደገና የጣት አሻራዎችዎ ይወሰዳሉ።

Eurodac የመረጃ ማዕከል የሚተዳደረው „eu-LISA“ የሚል ስያሜ ባለው የአውሮፓ ኅብረት ተቋም ነው። ከእርስዎ የሚገኙ መረጃዎች በሕጉ መሠረት ለተፈቀደላቸው ተግባራት ብቻ ነው የሚውሉት። እንዲሁም የእርስዎ መረጃዎች ለEurodac ማዕከል ብቻ ነው የሚላኩት። ወደፊት የጥገኝነት ማመልከቻ በሌላ የደብሊን-ሀገር የሚያስገቡ ከሆነ፣ የጣት አሻራዎችዎ ተወስደው በተመሳሳይ ሁኔታ ወደ Eurodac ይላካሉ። በEurodac የተከማቹት መረጃዎችዎ ከደብሊን-ሀገራት ውጭ ካሉ ሀገራትም ሆነ ተቋማት ጋር ልውውጥ አይደረግም።

1) የአውሮፓ ኅብረት ሀገራትን ማለት ነው፤ እነዚህም (ኦስትሪያ፣ ቤልጂየም፣ ቡልጋሪያ፣ ክሮኤሽያ፣ ሳይፕረስ (ቆጵሮስ)፣ ቼክ ሪፐብሊክ፣ ዴንማርክ፣ ኤስቶንያ፣ ፊንላንድ፣ ፈረንሳይ፣ ጀርመን፣ ግሪክ፣ ሃንጋሪያ፣ አየርላንድ፣ ጣልያን፣ ላትቪያ፣ ሊቱዌንያ፣ ሉክሰንቡርግ፣ ማልታ፣ ሆላንድ፣ ፖላንድ፣ ፖርቱጋል፣ ሩሜንያ፣ ስሎቫኪያ፣ ስሎቬንያ፣ ስፔን፣ ስዊድን፣ ኢንግላንድ፣ እንዲሁም አራቱ “ተባባሪ ሀገራት” ተብለው የሚጠሩት (ኖርዌይ፣ አይስላንድ፣ ስዊዘርላንድ፣ እና ልሽተንስታይን)።

©Europäische Union 2014
ይህን ጽሑፍ አባዝቶ መጠቀም ይቻላል። ፎቶዎችን በተናጠል አባዝቶ ለመጠቀም ከቅጅ መብት ባለቤቶች ፈቃድ ያስፈልጋል።



## መረጃ የሚገኝባቸው አድራሻዎች

የጥገኝነት ማመልከቻ የሚመለከተው ባለሥልጣን መሥሪያ ቤት (Asylbehörde)
Bundesamt für Migration und Flüchtlinge (BAMF)
Frankenstraße 210
90461 Nürnberg
ሥልክ: +49 (0)911 943 0
ፋክስ: +49 (0)911 943 10000
ኢሜል: service@bamf.bund.de

የEurodac መርማሪ አድራሻ
Bundeskriminalamt (BKA)
65173 Wiesbaden
ሥልክ: +49 (0)611 55 0
ፋክስ: +49 (0)611 55 12141
www.bka.de

ባለሥልጣን መሥሪያ ቤታችን፣ ሌላ ሀገር ውስጥ የጥገኝነት ማመልከቻ አስገብተው ሊሆን ይችላል፣ እናም ይህ የተባለው ሀገር ጉዳይዎን የመመልከት ኃላፊነት ሊኖረው ይችላል ብሎ ካሰበ፣ ስለሚከተለው የማጣራት ሂደት እና ይህም በእርስዎና በመብትዎ ላይ ሊያሳድር ስለሚችለው ተጽዕኖ ሰፊና ዝርዝር ማብራሪያ ይሰጥዎታል።

